# ከትምህርት ቤት ጎብኚ-እንግዶች፣ የሚጠበቁባቸው-ነገሮች

የሰራ-ላይ የዋለበት ቀን: ኦገስት (August) 4 ቀን 2023

## የፖሊሲ ጽሁፍ/Statement እና፣ ዓላማ

የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ በዓይነ-ህሊናው የሚያልመው-ዓለም፤ ሁሉም ተማሪ የተወዳጅነት ስሜትን፣ ፈተና ተቋቋሚነት፣ እና አዎታዊ ተጽዕኖ ላለው ማህበረሰብ እና በሕይወት ስኬት ለማበብ ዝግጁ የሚሆኑበት ዓለም እንዲሆን ነው። ተልዕኮአችን፣ ሁሉም ትምህርት ቤቶች - ተማሪዎች፣ ጤናማ መጋቢ ከሆነ ስፍራ ሆኖ፤ ጠንካራና አስደሳች በሆነ የመማር ተሞክሮዎች አማካኝነት፣ ወደተሟላ የስኬት እመርታቸው ላይ መድረሳቸውን ዋስትና-መስጠት ነው። DCPS፤ ከቤተሰቦች፣ የማህበረሰብ አባላቶች እና የዲስትሪክቱ - በሁሉቱም፣ በላቀ-ደረጃ እና በፍትሃዊነት ለመበልጸግ እየሰራ ለሁሉም DCPS ተማሪዎች ውጤታማነታቸውን ለማፋጠን ስልቶችን ከሚጠቀሙ-ኢጋሮች ጋር ግንኙነቶችን ለመገንባት — እና እያንዳንዱ ቤተሰብ መልካም-አቀባበልን እንዳገኘ እንዲሰማው እና እያንዳንዱ ልጅ ለመጎበት የሚያስፈልገውን ዕድሎች እና እርዳታን የሚያገኙበት ቦታ እንዲሆን፤ ቅድሚያ በመስጠቱ ኩራት ይሰማዋል።

ይህን ዓላማ በመደገፍ፤ DCPS ደህንነቱ-የተጠበቀ እና አዎንታዊ-የሆነ (positive) የትምህርት ቤት አካባቢዎች (school environments)ን ለሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች-ለማቅረግ በትትብር-ይሠራል። የዚህ ሰነድ ዓላማ፤ ለሁሉም ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ እና ወደ DCPS ትምህርት ቤቶች የሚመጡ ሌላ ጎብኚ-እንግዶች፤ የሚጠበቁ ስነምግባርን በቦታ-ለማስቀመጥ ዓላማ-አድርጎ የተዘጋጀ-ነው። እነዚህ-የሚጠበቁ ነገሮች፤ በሁሉም ግለሰቦች - በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ እና በDCPS ዝግጅት-ቦታ በሚሆኑ-ጊዜ ሁሉ በስራ-ላይ ይውላሉ።

## ስልጣን/Authority እና ተያያዥ-የሆኑ ፖሊሲዎች[1]

- DC Code § 38-174(c)(3)
- የትምህርት-ቤት ጎብኚ-እንግዳ (School Visitor) ፖሊሲ
- የትምህርት ቤት ማገጃ ማስታወቂያ ሂደቶች/School Barring Notice Procedures

## አጠቃላይ መርህዎች

DCPS፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ጎብኚ-እንግዶች፣ የሚከተሉትን እንዲረዱ እና እንዲያከብሩ ይጠብቃል:

- የDCPS ሠራተኞች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች - ሁሉም ልጆች፣ ደህንነቱ-በተጠበቀ አካባቢ ውስጥ እንዲማሩ ይፈልጋሉ።
- የDCPS ሠራተኞች እና ወላጅ/አሳዳጊዎች፤ ለሁሉም ተማሪዎች ጥምቅ-ለማስገኘት መስራት-አለባቸው።
- ሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ጎብኚ-እንግዶች፣ እንዲሁም ሁሉም የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላቶች፤ ከአክብሮት-ጋር መያዝ-አለባቸው።
- ስጋቶች-ሲኖሩ፣ በመጀመሪያ ወደ ትምህርት ቤቱ ሊነገሩ-ይገባቸዋል። ስጋቶቹ በትምህርት ቤቱ ሊወገዱ ካልቻሉ፤ አቤቱታዎችን ፋይል-ለማድረግ እና መፍትሄ ለማስገኘት - በርካታ ሂደቶች አሉ። (ከዚህ-በታች የግጭት/አለመግባባት፣ ማስወገድ/Dispute Resolution ክፍል (section)ን፣ ተመልከቱ)።

የትምህርት ቤት ሠራተኞች እና አስተዳደር፤ ወዲያውኑ ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ለመነጋገር ሁልጊዜ-ላይገኙ ይችሉ ይሆናል። በቅድሚያ ቀጠሮ-መያዝ - ከሠራተኛ አባሉ ጋር ወይም ከአስተዳደር ጋር ለመነጋገር - መገኘታቸው የማረጋገጫ ብቸኛ መንገድ ነው። የDCPS ሠራተኞች፤ ሁሉንም የስልክ ጥሪዎች እና ኢሜሎች ወዲያውኑ ምላሽ-መስጠት ይጠበቅባቸዋል። የስልክ-ጥሪዎች እና ጉብኝቶች/visits - ወዲያውኑ ከእናንተ-ጋር ሊነጋገር የሚችል ሰው ከሌለ ፤ ምላሽ-ይሰጠዋል።

---

[1] በአሁኑ-ጊዜ ያሉት የDCPS ፖሊሲዎች በዚህ-ይገኛሉ https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

## በስጋቶች-ላይ መፍትሄ ለመስጠት፣ ተመራጭ-የሆኑ ልምምዶች እና የተለመዱ-ነገሮች

**ጉዳዩን ወይም እየገጠማችሁ ያለውን ችግር፣ በግልጽ ተናገሩ።** ለመጠየቅ-የምትፈልጉትን የጥያቄዎች ዝርዝር-ፃፉ። ስጋታችሁን ሊያስወግድ ይችላል-ብላችሁ የምታስቡትን - በርካታ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ለዩ።

**ተረጋግታችሁ-ቆዩ (Stay calm)።** ትኩረታችሁን በእውነታው-ላይ አድርጉ-እንጂ፤ ስለጉዳዩ ከምትነጋገሩት-ሰው ጋር አታድርጉት። አክብሮትን የምታሳዩ ሆናችሁ መቀጠል እና ጥሩ-ዓላማ ያላቸው መሆኑን መገመት።

**የተረዳችሁትን-ነገር፣ ማብራራት (Clarify your understanding)።** ስለ አንድ-ነገር እርግጠኛ-ካልሆናችሁ ወይም የሰማችሁትን ነገር በደንብ ካልተረዳችሁ፤ ማብራሪያ እና እንደገና-እንዲገለጽላችሁ ጠይቁ። ስለ ሁኔታው - የሌላኛውን-ሰው ሁኔታ ለመመልከት እና ሊያቀርቡት የሚችሉትን መፍትሄዎች ለመረዳት ሞክሩ።

**አማራጭን-የምትቀበሉ ሁኑ (Be flexible)።** ችግሮች፣ ከአንድ-በላይ በሆኑ መንገዶች መፍትሄ ሊገኝላቸው እንደሚችል ማወቅ። አማራጭ-የሆኑ መፍትሄዎችን ለመቀበል ክፍት-ሁኑ።

**ሰነዶች/recordsን አስቀምጡ።** የስብሰባ ቀናቶችን እና ሰዓታትን፣ ከማን-ጋር እንደተነጋገራችሁ፣ እና ስለምን-እንደተወያያችሁ፤ በማስታወሻ-መያዝ። የደብዳቤዎችን፣ የቅጾችን እና ሌላ ከስጋታችሁ-ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቁሳቁስ/material - ቅጂያቸው/copiesን አስቀምጡ።

## የተከለከሉ ባህሪያቶች

አዎንታዊ-የሆነ እና ደህንነቱ-የተጠበቀ የትምህርት ቤት አካባቢን ለማቅረብ እንዲቻል፤ የሚከተሉት ባህሪያቶች - በወላጆች/አሳዳጊዎች፣ በጎብኚ-እንግዶች፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ እና በአጠቃላይ የሕዝቡ አባላቶች እንዳይደረጉ፣ DCPS ይከለክላል:

- ጥቃት-ፈጣሪ/Abusive፣ የሚያስፈራራ፣ የብልግና ወይም ወከባ-የሚፈጥር ግንኙነት/communicationን - ወይ-በአካል (in person)፣ በኢሜል፣ በቴክስት (text)/በድምጽ-መልዕክት (voicemail)/በስልክ፣ ወይም-ደግሞ በሌላ የጽሁፍ ወይም የቃል ግንኙነት-ማድረጊያ
- በDCPS ከንውኖች-ላይ፣ በመማሪያ-ክፍል የሚደረገው የተሳካ-ከንውንን፣ የተቀጣሪ-ሠራተኛን ቢሮን ወይም የስራ-ቦታን፣ የካምፓሱን እንግዳ-መቀበያ አካባቢ/campus lobby ወይም የትምህርት ቤቱን ግቢ ጨምሮ - የስፖርት ዝግጅቶችን፣ የመኪና-መቆሚያ ቦታዎችን እና የተማሪ መውረጃ (drop-off)/መውሰጃ (pick-up) ቦታዎችን አካትቶ - መስተጓጎልን ወይም ለማስተጓጎል ማስፈራራትን የሚያካትት፣ እክል-ፈጣሪ ባህሪይ
- የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኛን፣ ጎብኚ-እንግዳ (visitor)ን ወላጅ/አሳዳጊ፣ ወይም ተማሪን፤ ማስፈራራት
- የDCPS ንብረትን፣ ተቀጣሪ-ሠራተኛን፣ ጎብኚ-እንግዳ (visitor)ን፣ ወላጅ/አሳዳጊ፣ ወይም ተማሪ ላይ ውድመት-ለማድረግ ማስፈራራት
- የሌላን-ሰው ልጅ በጉዳዮች ላይ ለመወያየት ወይም ለእነርሱ ተግሣፅ-ለመስጠት መቅረብ
- የትምህርት ቤት ንብረት/school propertyን ማበላሸት ወይም ጥፋት-ማስከተል
- ለአትሌቲክ/athletic ዝግጅቶች እና የትምህርት ቤት ማሳያ-ፕሮግራሞች ካልሆነ-በስተቀረ፤ መቅዳት ወይም በቪዲዮ-ቴፕ፣ ማንኛውንም ተማሪ - በትምህርት ቤት ግቢዎች ውስጥ መቅዳት
- ስም-አጥፊ (Defamatory)፣ ጸያፍ፣ ወይም አዋራጅ አስተያየቶችን - ስለ ትምህርት ቤት ወይም ስለ ትምህርት ቤት ሠራተኞች - ለሕዝብ ወይም ለሌላ-ሰው የሚታይ-ማድረግ
- ማህበራዊ-ሚዲያ (social media) - ሌሎችን ለማንጓጠጥ (to bully)፣ ጥቃት-ለማድረስ ወይም ለማዋረድ፤ ወይም በትምህርት ቤቶች ላይ ዘመቻ ለማቀጣጠል እና አቤቱታ-ለመፍጠር፤ እና/ወይም በሌሎች ወላጆች/ተማሪዎች ላይ በማህበራዊ አውታረ-መረብ (networking) እና በድህረ-ገጾች አማካኝነት - አለአግባብ-መጠቀም[2]
- ማስፈራራት፣ ጥቃት-ፈጣሪ መሆን፣ ወይም ሌላን ሰው በተሳሳተ አመለካከት - በዘር፣ በቀለም፣ በመጡበት-የማንነት መነሻ፣ በዜግነት ሁኔታ፣ በጋብቻ-ሁኔታ፣ በሃይማኖር፣ በእድሜ፣ በፆታ፣ በፆታ አገላለጽ፣ በፆታዊ-ግንዛቤ፣ በጉዳተኝነት፣ ወይም በእድሜ አድልዎ ማድረግ
- በትምህርት ቤቱ ቅጥር-ግቢ ክፍል-በሆነው ቦታው ውስጥ - ካለፈቃድ መግባት፣ ወይም በማንኛውም ህንፃ ወይም ተቋም ውስጥ - መደበኛ-ጊዜው አልቆ-ከተዘጋ በኋላ መቆየት
- በDCPS ንብረት ውስጥ ወይም በDCPS ዝግጅት ላይ፣ የማንኛውንም-ሰው ነፃ የሆነ ንቅናቄ ማገድ

---

[2] ይህ የሚያካትተው - ማንኛውንም የማህበራዊ ሚዲያ (social media) መገናኛን - እነዚህን-ጨምሮ ነገር ግን በነዚህ-ብቻ ሣይወሰን፤ 'ድህረ-ገጾች/websites፣ ብሎግስ/blogs፣ ዊኪስ/wikis፣ እና የማህበራዊ ኔትወርኪንግ ገጾች - እንደ፤ ፌስቡክ/Facebook፣ ኢንስተግራም/Instagram፣ ቲክቶክ/TikTok፣ ስናፐቻት/Snapchat፣ ሊንክዲን/LinkedIn፣ ትዊተር/Twitter፣ ወዘተ...

- የትራፊክ ሕጎችን፣ የመኪና-ማቆሚያ ደንቦችን፣ ወይም ለሌላ በተሽከርካሪ-ላይ የተደረጉ እገዳዎችን - በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ በሚሆኑበት-ጊዜ መጣስ
- የትምህርት ቤት መጓጓዣን-መረበሽ ወይም የመጓጓዣ አገልግሎት ሠራተኞችን በአውቶቡስ-ውስጥ፣ በመንገድ-ላይ፣ በአጎራባች-ሰፈሮች ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ግቢዎች ውስጥ - ፊለፊት-ገጥሞ መከራከር
- በትምህርት ቤት ንብረት ወይም በትምህርት ቤት ክንውን-በሚካሄድባቸው ቦታዎች ላይ፣ በአልኮል-መጠጥ ወይም ቁጥጥር በሚደረግባቸ ዕፆች ስር መሆን ወይም፣ ይዞ-መገኘት፣ መጠቀም፣ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ መለዋወጥ
- በትምህሀት ቤት ንብረት-ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ክንውን-በሚካሄድበት ቦታ፣ ትንባሆ/tobacco መጠቀም
- በትምህሀት ቤት ንብረት-ውስጥ ወይም በማንኛውም የትምህርት ቤት ዝግጅት ላይ፣ ከሕግ-አስከባሪ ሹሞች በስተቀረ - የጦር መሣሪያዎችን መጠቀም ወይም መያዝ
- የሚታወቅ - ማንኛውም የDCPS ሠራተኛ - ስራቸውን በሚያከናውኑበት-ጊዜ፤ ማንኛውም ተገቢ-የሆነ ጥያቄ በሚቀብ-ጊዜ ተገዢ ለመሆን እምቢተኛነትን ማሳየት
- ማንኛውንም የፌደራል ወይም የስቴት ሕግን ወይም ፖሊሲን - በትምህርት ቤቱ ንብረት ውስጥ በሚሆኑ ጊዜ - ወይም በትምህርት ቤት የክንውን-ዝግጅት ላይ በሚሆኑ ጊዜ መጣስ
- ማንኛውንም ከዚህ-በላይ የተዘረዘሩትን የተከለከሉ-ድርጊቶችን - ሌሎችን እንዲያደርጉ ሆን-ብሎ ማነሳሳት

## የሚያስከትለው-መዘዝ/Consequences

እንደ ክስተቱ ክፉኛ-ከባድ መሆን ላይ መሠረት-በማድረግ፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ጎብኚ እንግዶች (visitors)፣ የትምህርት ቤቱን ግቢ ወዲያውኑ-ለቅቀው እንዲወጡ ሊጠየቁ-ይችላሉ። ትምህርት ቤቶች በተጨማሪም፤ ግለሰቦችን ከDCPS ካምፓሶች እና ዝግጅቶች፣ በትምህርት ቤት ማገጃ ማስታወቂያ ሂደቶች/School Barring Notice Procedures ውስጥ በተዘረዘርው ሂደት-አማካኝነት፤ መታገድን ሊጠይቁ-ይችላሉ።

በተጨማሪም፤ በትምህርት ቤት ጎብኚ-እንግዳ ፖሊሲ/School Visitor Policy ስር - ከባድ-የሆነ ክስተት ተፈጥሮ - የተማሪዎችን እና የሠራተኞችን ደህንነትን እና የደህንነት-ጥበቃን በአደጋ-ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ካለ፣ ወይም የትምህርት ቤቱን የትምህርት-አሰጣጥ፣ ክንውን፣ ወይም እንቅስቃሴውን ሊያውኩ-የሚችሉ ሁኔታዎች በህንፃው ከተፈጠረ በኋላ፤ ለሁሉም ጎብኚ-እንግዶች (visitors) ጊዜያዊ-ወደ ህንፃው የመግቢያ-ፈቃድን ለመገደብ - ሊጠይቅ ይችላል።

## ግጭት/አለመግባባት፣ የማስወገጃ አማራጮች

የ**'ሃቀኝነት ቢሮ (Office of Integrity (OI)'** የወላጅ/አሳዳጊ፣ ጎብኚ-እንግዳ፣ እና የተማሪ አቤቱታዎችን፣ ቅሬታዎችን ጊዜውን-በጠበቀ እና በቅልጥፍና እርዳታ-ለማድረግ፣ የDCPS ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን በተሻለ-ሁኔታ ለማገልገል፤ ሁሉንም-አገልግሎት በአንድ-ቦታ የሚያገኙበት ቦታ-ነው። ስለ 'የሃቀኝነት ቢሮ (Office of Integrity)፣ የበለጠ ለማወቅ እና ለማነጋገር:

- በhttps://dcps.dc.gov/page/office-integrity ላይ ጎብኙ (የኦንላይን የመመራት (Referral) ቅጽን ማስገባትም የምትችሉት እዚህ-ነው)፣
- ኢሜል dcps.cio@k12.dc.gov, ወይም
- በስልክ (202) 939-4913 ደውሉ።

የ**'The Comprehensive Alternative Resolution & Equity (CARE) ቡድን'**፤ አድልዎ፣ ወሲባዊ ትንኮሳ (sexual harassment)፣ ማንጓጠጥ (bullying) ወይም ሌላ ተገቢ-ያልሆኑ ድርጊቶች፤ በተማሪ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ጎብኚ-እንግዳ - በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲገጥሙዋቸው፤ ቅሬታዎችን ለመቀበል እና ምርመራ-የማድረግ፤ ኃላፊነት አለበት። የ'CARE' ቡድን፤ ጊዜውን-በጠበቀ፣ ፍትሃዊነት-የሆነ፣ እና ሁሉን-አቀፍ በሆነ መንገድ፤ ችግሮችን ለመፍታት - ከትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር በመተባበር ይሰራል። ስለ 'CARE' ቡድን፣ የበለጠ ለማወቅ እና ለማነጋገር:

- በhttps://dcps.dc.gov/page/studentparentvisitor-grievance-process ላይ ጎብኙ (የኦንላይን የመመራት (Referral) ቅጽን ማስገባትም የምትችሉት እዚህ-ነው)፣
- ኢሜል dcps.care@k12.dc.gov
- ስልክ (202) 442-5405።

## እውቅናን-ማረጋገጫ ቅጽ

ለትምህርት ዓመት (SY) 2023-24፤ የትምህርት ቤት መሪዎች - ለጎብኚ-እንግዶች የሚጠበቁባቸው-ነገሮች (Expectations for Visitors) የሚለውን፣ ካሰራጩ በኋላ፣ ከትምህርት ቤት ማህበረሰባቸው ጋር፣ የሚከተሉትን የ'እውቅና-ማረጋገጫ ቅጽ/Acknowledgement Form' አማራጮችን - ሊጠቀሙ ይችሉ-ይሆናል። ለትምህርት ዓመት 2024-25 እና ከዚያ-ባለፈ፤ ይህ እውቅናን-ማረጋገጫ (acknowledgement) በDCPS የኦንላይን ምዝገባ ቁሳቁሶች/materials ውስጥ ይካተታሉ።

## እውቅናን-ማረጋገጫ ቅጽ (Acknowledgement Form)

### ከትምህርት ቤት ጎብኚ-እንግዶች (School Visitor) የሚጠበቁ-ነገሮች

DCPS፣ ለትምህርት ቤት ጎብኚ-እንግዶች (School Visitors) የሚጠበቅባቸውን-ነገሮች ቅጂ/copy መቀበሌን፣ እውቅና-በመስጠት አረጋግጣለሁ።

ከDCPS ጋር ያለኝ ግንኙነት/relationship: (የሚመለከተውን-በሙሉ እባካችሁ ምረጡ)

- ☐ ወላጅ/አሳዳጊ
- ☐ የበጎ-ፈቃደኝነት ስራ (Volunteer)
- ☐ ሌላ ጎብኚ-እንግዳ

ቀን: ___________________

ስም (ይፃፍ): ____________________________________________________________________________

ፊርማ: _________________________________________________________________________________